የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# ለ6ኛው ጠቅላላ ምርጫ ጥቅም ላይ የዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችና ሌሎች ልዩ ትኩረት የሚሹ ቁሳቁሶችና ሰነዶችን ለማስወገድ የተዘጋጀ ሰነድ

## የምርጫ ኦፕሬሽኖች መምሪያ

ታህሳስ 2014

አዲስ አበባ

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሰኔ 2013 እና መስከረም 2014 ላይ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ምርጫዎችን ያካሄደ ሲሆን ከዚያም በመቀጠል የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን እና ሌሎች ልዩ ትኩረት የሚሹ ቁሳቁሶችና ሰነዶችን የማስወገጃ አማራጮችን ገምግሟል።

የምርጫ ቁሳቁሶችና ሰነዶች ምደባ፣ ስርጭት፣ አጠቃቀም፣ ርክክብ፣ መልሶ ማምጣትን የሚመለከተው መመሪያ (ቁ. 8/2013) አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የሚከተለውን ይደነግጋል፡ "ለቅሬታ ወይም ለይግባኝ በማስረጃነት ሊያስፈልጉ የሚችሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችና ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ቁሳቁሶች ወይም ሰነዶች (ለምሳሌ የውጤቶች ማሳወቂያ ቅጾች ወይም ቃለ ጉባኤዎች) ሊወገዱ የሚችሉት፡ ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ፤ ከምርጫ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ማናቸውም አስተዳደራዊና ሕጋዊ ቅሬታዎች የመጨረሻ እልባት ካገኙ፣ ማንኛውም ዳግም-ቆጠራ ከተጠናቀቀና የምርጫ ውጤት የመጨረሻ ማረጋገጫ ከተሰጠው በኋላ ነው።"

ይህ ሰነድ የተለያዩ የማስወገጃ አማራጮችን እንደዚሁም ከአማራጮቹ ጋር የተያያዙ ሂደቶችን ይዘረዝራል። ሰነዱ አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 4 ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ይጠይቃል፣ ይህም የኢትዮጵያን የይግባኝ ህጋዊ መስፈርቶች እንዲሁም አለም አቀፍ ደረጃዎችን በሚመለከት የኦፕሬሽናል እና የሎጂስቲክስ መስፈርቶች ግምት ውስጥ መግባታቸውን ለማረጋገጥ ነው።

# የቁሳቁሶች ማስወገጃ ዘዴዎች

የምርጫ ቦርድ የኦፕሬሽን መምሪያ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን፣ ሌሎች ልዩ ትኩረት የሚሹ ቁሳቁሶችና ሰነዶችን በሙሉ በምርጫ ክልል ደረጃ ወይም በሌላ ቦታ በማቃጠል ቁሳቁሶችን የማስወገድ ስራ ያከናውናል።

### ጥቅም ላይ የዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችና ልዩ ትኩረት የሚሹ ሰነዶችን ማቃጠል

ጥቅም ላይ የዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ማቃጠል በምርጫ ክልል ደረጃ ይከናወናል። ይህ ቁሳቁሶቹን ለማስወገድ የሚያስችል ወጪ ቆጣቢ መንገድ ነው፣ ነገር ግን የዚህ ዘዴ ጉዳቱ ለአካባቢ ጥበቃ ተስማሚ አለመሆኑ ነው።

# ለአወጋገድ የተጠቀሙ የአሰራር ስርዓቶች

የሚከተሉት የአሰራር ስርዓቶች በመመሪያ 8/2021 የተካተቱትን የህግ ድንጋጌዎች እና በተለይም በመመሪያ 8/2021 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የታቀዱ ናቸው፤ የአንቀጹ ድንጋጌም፡ - "በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተመለከቱት ቁሳቁሶች በሙሉ ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ በቦርዱ ሰራተኞች ጥብቅ ክትትል እና እንደ አስፈላጊነቱ ታዛቢዎች በተገኙበት መልሶ ጥቅም ላይ ሊውሉ ወይም ሊወገዱ ይገባል።"

**የማስወገድ ተግባር ሃላፊነት:** ለዚህ አንቀጽ ትግበራ ሲባል፣ የሚመለከተው የምርጫ ክልልን የሚወክል ቢያንስ አንድ የምርጫ ክልል ሃላፊ ቁሳቁሶቹ ወደሚወገዱበት ቦታ ሲጓጓዙና አጠቃላይ ሒደቱ ሲከናወን በቦታው መገኘት አለበት። ይህ የማይቻል ከሆነ፣ የምርጫ ቦርድ የክልል ጽ/ቤት ሃላፊ ወይም ማንኛውም ቋሚ ሰራተኛ ሒደቱን በመምራት በአጠቃላይ ሒደቱ ወቅት መገኘት ይኖርበታል።

የምርጫውን ሂደት የሚመራው የምርጫ ቦርድ ሃላፊ የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል በማደራጀት የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን እና ሌሎች ሰነዶችን ለማስወገድ ከሚመለከተው ተቋም አስተዳደር ጋር መገናኘት አለበት።

**የቁሳቁሶች ደህንነት:** ቁሳቁሶቹ በፖሊስ መታጀብ አለባቸው። ፖሊስ አጠቃላይ የማስወገድ ሒደት ወቅት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የፖሊስ አባላትን መመደብና ሒደቱም ሲጠናቀቅ ነጭ (የድምፅ መስጫ) ሳጥኖችን አጅቦ ምርጫ ቦርድ ወደሚያሳውቀው አድራሻ ማድረስ አለበት።

**ክትትል/ትዝብት፡** በምርጫ ወቅት የተሳተፉት እጩዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች (ከምርጫው ራሳቸውን ያገለሉትም ቢሆኑ)፣ የምርጫውን ሂደት ለመታዘብ ዕውቅና የተሰጣቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የአካባቢ አስተዳደር ተወካዮች የድምፅ መስጫ ወረቀትና ሌሎች ቁሳቁሶች ሲወገዱ ተገኝተው መታዘብ ይችላሉ።

ምርጫ ቦርድ ሂደቱ ከመጀመሩ ቢያንስ 10 ቀናት ቀደም ብሎ ከላይ ለተጠቀሱት ባለድርሻ አካላት ጊዜና ቦታ የሚያሳውቅ ይሆናል እና ለመከታተልና ለመታዘብ የሚያስችሉ መስፈርቶችን ለእያንዳንዱ ምድብ ዝርዝር መመሪያ ይዘጋጃል።

የእጩዎች እና የተወካዮች እንዲሁም የታዛቢዎች መብትና ግዴታዎች በምርጫ ቦርድ ከተቀመጡት የታዛቢዎች መብትና ግዴታ ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው ይህ መብትና ግዴታ ለባለሥልጣናትም የጸና ይሆናል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ሌሎች ከላይ የተጠቀሱት አካላት በተገለጸላቸው ቦታና ጊዜ ካልተገኙ፣ ቦርዱ እነርሱ በሌሉበት የማስወገድ ሒደቱን ይቀጥላል።

## የሚወገዱ ቁሳቁሶች ዓይነት

1. የሕ/ተ/ም/ቤት የድምፅ መስጫ ወረቀት
2. የክልል ም/ቤት የድምፅ መስጫ ወረቀት
3. የሕዝበ ውሳኔ የድምፅ መስጫ ወረቀት
4. ጥቅም ላይ የዋሉና ያልዋሉ ቅጾች (የድምፅ መስጫ፣ የውጤቶች ቆጠራና ማዳመሪያ)

## ማስወገዱን ለመተግበር የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ተግባራት

### በዋና መ/ቤት፡

- ለምርጫ ክልል ኃላፊዎች ወይም ሌሎች ሃላፊዎች (በምርጫ ክልሉም ሆነ በማዕከል ደረጃ ላሉ) አወጋገድን እንዴት ማካሄድ እንደሚቻል የሚጠቁም የሥራ ሂደት መከታተያ ማዘጋጀት፣
- የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ለማጓጓዝ፣ ለማስወገድ እና ባዶ የድምፅ መስጫ ሳጥን ለመሰብሰብ የጊዜ ሰሌዳ ማውጣት፣
- ለክልል እና ለወረዳ አስተዳደሮች፣ ለፖሊስ፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች እና የማስወገድ ሒደቱ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ፤ ኦፊሴላዊ ግንኙነት መላክና የሚያስፈልጉ ነገሮችን መግለጽ (የሚቀርቡት ተቆጣጣሪዎች/ታዛቢዎች ዝርዝር ወዘተ)፣
- ክፍያዎችን ለማጠናቀቅ እና/ወይም የሚመለከታቸውን ሃላፊዎች ትራንስፖርት ለማዘጋጀት እንዲቻል ለማስወገድ ሒደቱ የተመደቡ ሰራተኞችን ዝርዝር ማዘጋጀት ናቸው።

**በመስክ ላይ አወጋገዱ በአካባቢ ደረጃ ከሆነ፡**

- ለእያንዳንዱ የምርጫ አይነቶች (ለሕ/ተ/ም/ቤት፣ ለክልል ም/ቤት እና ለሕዝበ ውሳኔ) 100 ያገለገሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለእያንዳንዱ ምርጫ ክልል እና 2 ጥራዝ ጥቅም ላይ ያልዋሉ (ለእያንዳንዱ ምርጫ አይነት) መምረጥና እነዚህን የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በማህደር ለማስቀመጥ ወደ አዲስ አበባ መላክ፣
- የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን የማቃጠያ ቦታ ለማዘጋጀት ከሃላፊዎች ጋር መወያየት፣
- የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን በተዘጋጀላቸው ቦታ ከሳጥኖች አውጥተው በተዘጋጀላቸው ቦርሳ ውስጥ የሚያስገቡ የጉልበት ሰራተኞችን መጠቀም፣
- ባዶ ነጭ (የድምፅ መስጫ) ሳጥኖች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ለምርጫ ቦርድ ዋና መ/ቤት መመለስ፣
- ለክልል መስተዳድር ሃላፊዎች የትራንስፖርት ትብብር ጥያቄ ማቅረብ፣
- ፖሊሶች እጀባ እንዲያደርጉና የማቃጠል ተግባር ሲከናወን በቦታው እንዲገኙ መጠየቅ፣
- አግባብነት ያላቸውን ቅጾች (ከቦርዱ በሚቀርበው መሰረት) በመሙላት የማስወገድ ሒደቱን በሰነድ መዝግቦ መያዝ ናቸው።

# የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን በማህደር ማስቀመጥ

የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብቻ በማህደር የሚቀመጡ ሲሆን ሌሎች ሰነዶች በሙሉ ይወገዳሉ።

## 1. በማሕደር የሚቀመጡ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን የመለየት ሒደት

**የሕዝበ ውሳኔ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች፡** የሕዝበ ውሳኔ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን በተመለከተ፣ በቦንጋ ከሚገኘው ጽሕፈት ቤት እንዲወገዱ ከተዘጋጁት መካከል 100 ጥቅም ላይ የዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች እና 5 ጥራዝ ጥቅም ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በመለየት ወደ ምርጫ ቦርድ ዋና መስሪያ ቤት ይላካሉ።

**የሕ/ተ/ም/ቤት እና የክልል ም/ቤት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች፡** እንዲወገዱ ከተዘጋጁት መካከል ለእያንዳንዱ የምርጫ ክልል 100 ጥቅም ላይ የዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለአንድ ውድድር እና 2 ጥራዝ ጥቅም ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በመለየት ወደ ምርጫ ቦርድ ዋና መስሪያ ቤት ይላካሉ።

ለእያንዳንዱ የምርጫ ክልል እና ለሕዝበ ውሳኔ፣ መክፈቱ የሚያስታውቅ ቦርሳ በመጠቀም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ወደ ምርጫ ቦርድ ዋና መ/ቤት ተጓጉዘው በማሕደር እንዲቀመጡ ይደረጋሉ፤ ይህ መከፈቱ የሚያስታውቅ ቦርሳ

በውስጡ የሕ/ተ/ም/ቤት እና የክልል ም/ቤት የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን የሚይዝ ሲሆን የቦንጋ ጽ/ቤትን በተመለከተ፣ የሕዝበ ውሳኔ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን የሚመለከት ይሆናል። ለዚህ ተግባር ጥቅም ላይ የሚውሉት መከፈታቸው የሚያስታውቅ ቦርሳዎች ከምርጫው ሒደት ተርፈው በመስክ ላይ የሚገኙት ሲሆኑ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች የምርጫ ክልሉን ስም፣ በውስጡ ያለውን ይዘትና የሚውልበት ተግባር (በማህደር እንዲቀመጥ) የሚል ማብራሪያ መከፈቱ በቦርሳው ፊት ለፊት ክፍል ላይ በማይጠፋ ማርከር መጻፍ አለባቸው፥ በርክክቡ ወቅትም አሁን ያለውን የርክክብ አሰራር በመከተል የቁሳቁስ መረካከቢያ ቅጽ ይሞላል።

## 2. የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን በምርጫ ቦርድ ዋና መ/ቤት በማሕደር ማስቀመጥ

የድምፅ መስጫ ወረቀት የያዙ እና መከፈታቸው የሚያስታውቅ ቦርሳዎች ወደ ዋና መ/ቤት እንደደረሱ፣ በየክልሉ የሚደለደሉ/የሚደራጁ እና የሚቀመጡ ይሆናል።

ምርጫ ቦርድ እነዚህን መከፈታቸው የሚያስታውቅ ቦርሳዎች ባሉበት እንዲቆዩ ሊያደርግ ወይም ከእያንዳንዱ ክልል እና ውድድር (ሕዝበ ውሳኔን ጨምሮ) 1 የድምፅ መስጫ ወረቀት በመለየት በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑና ምክክር እንዲደረግባቸው ራሱን ችሎ በተዘጋጀ ማህደር ውስጥ እንዲቀመጡ ማድረግ ይችላል። ይህ ከሆነም መከፈታቸው የሚያስታውቁት ቦርሳዎች ከቀሩት ቁሳቁሶች ጋር በሰማያዊ ሳጥኖች ውስጥ የሚቀመጡ እና ክልሉ/ምርጫ ክልሎቹ በግልጽ እንዲታወቁ ሳጥኖቹ ላይ ገላጭ ፅሑፍ ይጻፋል።

# የማስወገጃ ጊዜ ሰሌዳ

የምርጫ ቁሳቁሶችና ሰነዶች ምደባ፣ ስርጨት፣ አጠቃቀም፣ ርክክብና መልሶ መሰብሰብን የሚመለከተው መመሪያ (ቁ. 8/2013) አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 4 ላይ "ማንኛቸውም ልዩ ትኩረት የሚሹ  የምርጫ ቁሳቁሶች ወይም ሰነዶች የሚከተሉት ሒደቶች ሲጠናቀቁ መወገድ አለባቸው ይላል፡-

*ሀ. ከላይ የተጠቀሱት ኹነቶች ወይም ውሳኔዎች በሙሉ ሲጠናቀቁ፤ ወይም*

*ለ. ከድምፅ መስጫ ቀን አንድ ዓመት በኋላ።"*

አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 4፣ ተ.ቁ ሀ ከሁሉም ዓለም አቀፍ መስፈርቶችና የኢትዮጵያ የሕግ ማዕቀፍ ጋር የሚጣጣም ሲሆን እና የወንጀል ምርመራ የሚደረግበት አግባብ በማይኖርበት ጊዜ የሚከተለው ሃሳብ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።

1. አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 4፣ ተ.ቁ ለ የመጨረሻው የተረጋገጠ ውጤት ከተገለጸ ከስድስት (6) ወራት በኋላ በሚል የተቀየረ ሲሆን ምክንያቶቹም የሚከተሉት ናቸው፡-

- ለ "ይግባኝ" በሕግ የተፈቀደው ጊዜ ከ6 ወር የማይበልጥ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ፡
  - ✓ አንድ ይግባኝ ባይ የምርጫ ቦርድ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችለው የመጨረሻው የተረጋገጠ ውጤት ከተገለጸ ከ**10 ቀናት** በኋላ ይሆናል፤
  - ✓ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የ **1 ወር** ጊዜ ይኖረዋል፤
  - ✓ ይግባኝ ባይ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት ለመቅረብ የ **2 ወራት** ጊዜ ይኖረዋል፤
  - ✓ ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት የ **2 ወራት** ጊዜ ይኖረዋል (ይህ ውሳኔ በሕግ የተቀመጠ ይርጋ ቢኖርበትም፣ ያለውን አሰራር በማየትና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው 1 ወር በመሆኑ፣ እኛ 2 ወር እንዲሆን ሃሳብ አቅርበናል)
  - ✓ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልል ጽ/ቤቶች ቢሮዎቻቸው ጊዜያዊና ከመንግስታዊ አስተዳደር የተሰጡ ሲሆኑ መስተዳድሮችም ምርጫ ክልሎች ቢሮዎቹን በተቻለ ፍጥነት እንዲመልሱ ጠይቀዋል፤
  - ✓ የምርጫ ክልል ክፍያዎችን ለማጠናቀቅ፣ ሁሉም ሰጥኖች ወደ ዋና መ/ቤት መመለስ ይኖርባቸዋል፤
  - ✓ የድምፅ መስጫ ሰጥኖችና ሌሎች ልዩ ትኩረት የሚሹ ቁሳቁሶች በመስክ ላይ በቆዩ ቁጥር፣ ቁሳቁሶቹ ላልተገባ አገልግሎት የመጋለጥ ዕድላቸው ይበልጥ የሚጨምር በመሆኑ ነው።

2. አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 4፣ ተ.ቁ ሐ እንደሚከተለው ተጨምሯል፡ "ምርጫ ቦርድ ምርጫ በተካሄደባቸውና እንደዚሁም ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድባቸው ተወስኖ ድጋሚ ምርጫውም ተካሂዶ ውጤታቸው የተገለጸባቸው የምርጫ ክልሎችን የድምፅ መስጫ ወረቀቶችና ልዩ ትኩረት የሚሹ ቁሳቁሶችን ማስወገድ ይችላል።"

ከሰኔ 2013 እስከ መስከረም 2014 ድረስ ለተካሄዱት ምርጫዎች፣ በሃገሪቱ ውስጥ ያለውን የፀጥታ ሁኔታ እና በዋና መ/ቤት ደረጃ ያለውን የመጋዘን እጥረት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ቁሳቁሱን የማስወገዱ ተግባር ከጥር ወር መጨረሻ እስከ የካቲት አጋማሽ ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲከናወን ቦርዱ ወስኗል።